በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁጥር** - 226658

ታህሳስ 24 ቀን 2015 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሲቲ አሰፋ አብደላ- ጠበቃ ሲሳይ ሃይሉ -ጠበቃ እንዳልካቸው ሙላው - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** አቶ ራህመቶ ሽኩራ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

**ፍርድ**

ጉዳዩ አንድ ክስ በድጋሚ የቀረበ ነዉ ወይም ተከፋፍሎ የቀረበ ነዉ ሊባል የሚችልበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመጣጡም ሲታይ ክርክሩ በተጀመረበት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ በመካከላቸዉ በተደረገዉ የንብረት ክፍፍል ክርክር መነሻነት ፍርድ ቤቱ የካቲት 27 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ለኮንዶሚኒየም ዕጣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዝግ አካዉንት ሲቆጥቡ የነበረዉን ገንዘብ እንዲካፈሉ ዉሳኔ በሰጠበት ዕለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባወጣዉ ዕጣ ከተጠሪ ጋር በጋራ በቆጠቡት ገንዘብ መሠረት ባለሁለት መኝታ ኮንዶሚኒየም ቤት በዕጣ የደረሳቸዉ መሆኑን በ2013 ዓ.ም ያወቁ መሆኑን ጠቅሰዉ ኮንዶሚኒየሙ የጋራ ሀብት ነዉ ተብሎ ይወሰንላቸዉ ዘንድ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ላይ የኮንዶሚኒየም ቤት ለማግኘት ተመዝግበን የቆጠብነዉ ገንዘብ ጋብቻ እስኪፈርስ ድረስ በየወሩ የተቆጠበ ገንዘብ እንካፈል በማለት አመልካች ለጠየቁት ዳኝነት ተጠሪ በሰጠሁት መልስ የኮንዶሚኒየም ዕጣ የእኔ ሆኖ እንዲቀጥል የሚል ክርክር አቅርቤ ክርክር ከተደረገ በኋላ ዉሳኔዉ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ ከተቆጠበ ገንዘብ ዉስጥ ግማሹን አመልካች እንዲካፈሉ የተሰጠ ዉሳኔ ያልተሻረ መሆኑን ጠቅሰዉ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በተጠሪ የቀረበዉን የመጀመሪያ መቃወሚያ መርምሮ አመልካች በግራ ቀኝ መካከል ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በቀድሞ መዝገብ ላይ በተደረገ ክርክር የኮንዶሚኒየም ቤት ለማግኘት በተጠሪ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በየወሩ የተቆጠበ ገንዘብ ከጋራ ገቢ የተገኘ መሆኑን ጠቅሰዉ ያቀረቡትን ዳኝነት መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤቱ በተጠሪ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለኮንዶሚኒየም ቤት ቁጠባ ተብሎ ዉሳኔ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ ከተቆጠበ ጠቅላላ ገንዘብ ግማሹን አመልካች እንዲካፈሉ ዉሳኔ መስጠቱን፤ የኮንዶሚኒየም ቤት ቁጠባ ገንዘብ ዉጤቱ ቤት ማግኘትን የሚያስከትል ሲሆን አመልካች የምፈልገዉ ገንዘብ ነዉ በማለት ዳኝነት ጠይቀዉ ፍርድ ቤቱ በዚያዉ መሠረት መወሰኑ ተገቢ ሆኖ ተጠሪ የኮንዶሚኒየም ዕድልን በተመለከተ ክርክር አቅርበዉበት እያለ ፍ/ቤቱ በዝምታ ማለፉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 5(3) መሠረት እንደተነፈገ የሚቆጠር በመሆኑ የአመልካች ዳኝነት በድጋሚ የቀረበ ነዉ ሊባል የሚችል መሆኑን፤ ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ቀድሞ እንዲከፈላቸዉ መብት ባገኙበት የቁጠባ ገንዘብ ሊያገኝ የሚችለዉ መብት ላይ ዉጤት ያለዉ መሆኑን አመልካች እየተረዱ መጠየቅ ሲችሉ ሆን ብለዉ ያስቀሩት የኮንዶሚኒየም ዕድል ዳኝነት ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 216(3) ዉድቅ ነዉ በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ላይ ሲሆን፣ አመልካች ግንቦት 08 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈዉ በጠበቃቸዉ አማካይነት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ፍርድ ባላረፈበት ንብረት ላይ የመጨረሻ ፍርድ ተሰጥቷል በሚል እንዲሁም አመልካች የኮንዶሚኒየሙን ዳኝነት ጉዳይ ከቀደመዉ ዳኝነት ጋር መጠየቅ ሲችሉ ሆን ብለዉ የተዉት አለመሆኑ እየታወቀ የስር ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 5 እና 216(3) ድንጋጌ ያላግባብ በመጥቀስ ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን ባልና ሚስት በጋራ ጥረታቸዉ ያፈሩት የጋራ ሀብት ከነፍሬዉ እኩል ሊካፈሉ ይገባል የሚለዉን የቤተሰብ ህግ መርህ የሚጥስ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ታርሞ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ተመርምሮም ዕጣዉ አስቀድሞ ቢደርስ ኖሮ ቤቱ የጋራ መባሉ ባላከራከረበትና የተቆጠበዉን ገንዘብ አመልካች በዉሳኔዉ መሠረት ባልወሰዱበት ሁኔታ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ሐምሌ 06 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች የጠየቁትን ዳኝነት መሠረት በማድረግ ለኮንዶሚኒየም ዕጣ የተቆጠበዉን ገንዘብ ግማሹን እንዲካፈሉ በሚል ቀደም ሲል ፍርድ ቤቱ ዉሳኔ መስጠቱንና ዉሳኔዉም እንዲፈጸም አመልካች በጠየቁት መሠረት ለፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ትዕዛዝ መስጠቱን፤ ዕጣዉ የደረሰዉ ጋብቻዉ ከፈረሰ በኋላ መሆኑን፤ የኮንዶሚኒየም ዕጣን በተመለከተ ተጠሪ ቀደም ሲል ክርክር ተደርጎ አመልካች ይህን አስመልክቶ የጠየቁት ዳኝነት አለመኖሩን፤ በመሆኑም አመልካች በድጋሚ ያቀረቡትን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 5 እና 216(3)

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ*
*ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ድንጋጌዎችን እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 46606 ላይ የተሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ጸንቶ እንዲወሰንላቸዉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት ለኮንዶሚኒየም ዕጣ እንዲዉል በባንክ የተቆጠበ ገንዘብ ድርሻቸዉን እንዲካፈሉ የሚል ዉሳኔ በተሰጠበት ቀን የኮንዶሚኒየም ዕጣ መዉጣቱንና ዕጣዉ መዉጣቱንም ያወቁት ከዚያ በኋላ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ ተጠሪ ይህን ፍሬ ነገር ሳይክዱ ክሱ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል ብለዉ በስር ፍርድ ቤት የተከራከሩ እና አሁንም አጥብቀዉ የሚከራከሩት ለዕጣዉ ዓላማ የተቆጠበዉ ገንዘብ አመልካች ድርሻቸዉን እንዲካፈሉ የተሰጠ ዉሳኔ ጸንቶ ያለ እና አፈፃፀምም የቀረበበት መሆኑን እንዲሁም አመልካች የኮንዶሚኒየም ዕጣ ጭምር መጠየቅ እየቻሉ ሆን ብለዉ በተዉት ነገር ላይ ዳኝነት መጠየቅ የማይችሉ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች አንድ ደረጃ ላይ ሲደርሱ መቋጫ ሊያገኙ ይገባል የሚለዉ መርህ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ መሠረታዊ መርሆዎች ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ድጋሚ ክስ እንዳይቀርብ እና ክርክሮች ተነጣጥለዉ እንዳይቀርቡ በመከልከል በአንቀጽ 5 እና አንቀጽ 216 ላይ በየቅደም ተከተላቸዉ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ መርህ መሠረት በማድረግ የተቀረጹ ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡ የሁለቱ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ዓላማ በአንድ ጉዳይ ላይ ተደጋጋሚ ክርክሮች እንዳይቀርቡ ወይም ከቀደመዉ ክርክር ጋር መቅረብ ይችሉ የነበሩ ክርክሮች ተነጣጥለዉ እንዳይቀርቡ በማድረግ ክርክሮች መቋጫ እንዲኖራቸዉ ማድረግ (finality of litigation) ቢሆንም በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ልዩነት ያለ መሆኑንም መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡

በህጉ አንቀጽ 5 መሠረት አንድ ክስ በድጋሚ የቀረበ ነዉ ለማለት ለቀረበዉ ክስ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ አስቀድሞ በህግ ስልጣን ለተሰጠዉ ፍርድ ቤት ቀርቦ የመጨረሻ ፍርድ የተሰጠበት መሆኑን፣ በቀረበዉ ክስ መሠረት የሚያዘዉ ጭብጥ እና የክርክሩ ሥረ ነገር ቀድሞ ከተወሰነዉ ጋር አንድ ዓይነት መሆኑ፣ በቀረበዉ ክስ የሚከራከሩት ሰዎች በቀደመዉ ክስ ተከራካሪ የነበሩ ወይም በቀደመዉ ክርክር ተከራካሪ ከነበሩት መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች መሆናቸዉን ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለዉ ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያዉ ክርክር ላይ በአንደኛዉ ወገን ተጠይቆ በሌላኛዉ ወገን የተካደ ወይም በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተካደ እና በዚህ ጉዳይ ላይም ዉሳኔ የተሰጠበት ወይም ሊሰጥበት ይገባ የነበረ መሆኑንም መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል አንድ ክስ ከቀደመዉ ክስ ጋር ተጠቃሎ መቅረብ ሲገባዉ ተነጣጥሎ የቀረበ ነዉ በሚል ምክንያት ዉድቅ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ በህጉ አንቀጽ 216 ላይ የተመለከተ ሲሆን፣ ይህ ድንጋጌ በአጠቃለይ ስለ ክስ አቀራረብና አገላለጽ የሚመለከት ነዉ፡፡ አንድ ከሳሽ ክስ ሲያቀርብ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ መቅረብ እንደሚገባ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ የተመለከተ ሲሆን ንዑስ ቁጥር 3 ደግሞ አንድ ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረዉ ሀብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ለማቅረብ እንደማይፈቀድለት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም አንድ ክስ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 216(3) መሠረት ዉድቅ ሊሆን የሚችለዉ ከሳሽ ክሱን ሲያቀርብ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑ ነገሮች በሙሉ አጠቃሎ ማቅረብ ሲችል ሆነ ብሎ ቀንሶ ያስቀረዉ መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡ ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰዉ ክሱን አጠቃሎ ማቅረብ ሲችል ሆን ብሎ አስቀርቶታል በሚል

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ምክንያት ክሱ ዉድቅ ሊደረግ የሚገባ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ከሳሽ የመጀመሪያ ክሱን ሲያቀርብ ከክሱ ጋራ ተጠቃሎ ሊቀርብ የሚገባዉ የበሰለ መብት ወይም የክስ ምክንያት የነበረ መሆን አለመሆኑን መሠረት በማድረግ መመርመር ያስፈልጋል፡፡

ይህን ሁሉ እንደ አጠቃላይ ይዘን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ አመልካች በቀደመዉ ክስ የጠየቁት ዳኝነት ለኮንዶሚኒየም ዕጣ ዓላማ የተቀጠበ ገንዘብ እንዲካፈሉ እንዲወሰንላቸዉ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በመጨረሻ ላይ የሰጠዉ ዉሳኔም ለኮንዶሚኒየም የተቀጠበዉን ገንዘብ ይካፈሉ የሚል ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ የኮንዶሚኒየም ዕጣ ከወጣ ቤቱ የጋራቸዉ እንዲሆን እንዲወሰን በአመልካች በኩል የተጠየቀ ዳኝነት የለም፤ በዚህ ረገድ የተሰጠ ዉሳኔም የለም፡፡ በቀደመዉ ዉሳኔ ተይዞ እልባት የተሰጠዉ ጭብጥ ከተጠሪ ጋር በጋራ የቆጠቡት ገንዘብ ግራ ቀኝ ሊካፈሉ የሚገባ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት እንጂ ዕጣ የወጣበት ኮንዶሚኒየም ቤት አመልካች እና ተጠሪ ሊካፈሉ ይገባል ወይስ አይገባም የሚል የክርክር ጭብጥ አልነበረም፡፡ ስለሆነም አንድ ክስ በድጋሚ የቀረበ ነዉ ሊባል የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ከፍ ሲል በተመለከተዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 5(1) ላይ የተመለከተዉን የሚያሟላ አይደለም፡፡ ከላይ እንደተገለጸዉ የስር ፍርድ ቤት ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርስ ተጠሪ የኮንዶሚኒየም ዕጣን በተመለከተ ክርክር አቅርቦ ዉድቅ መደረጉ በህጉ አንቀጽ 5(3) ላይ በተመለከተዉ መሠረት እንደተነፈገ ይቆጣራል የሚል ምክንያት በመጥቀስ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ በቀድሞዉ ክርክርና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ተቀባይነት ሳያገኝ የታለፈ ጉዳይ እንደተከለከለ እንደሚቆጠር የሚደነግግ ሲሆን፣ ዓላማዉም በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጉዳዩ ዳኝነት ያልተሰጠበት ከሆነ ከሳሹ ወገን ዳኝነቱን እንደተነፈገ ቆጥሮ ዳኝነቱን መነፈጉ የሚጎዳዉ ከሆነ መብቱን በይግባኝ ማስከበር እየቻለ ይህን ሳይጠቀም በዚያዉ ጉዳይ ላይ ድጋሚ ዳኝነት እንዳያቀርብ ለመከልከል ነዉ፡፡ ይሁንና በተያዘዉ ጉዳይ የኮንዶሚኒየም ዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆን እንዲወሰንለት በቀደመዉ ክርክር ዳኝነት የጠየቁት ተጠሪ እንጂ አመልካች አይደሉም፡፡ በመሆኑም ይህ ድንጋጌ ለተያዘዉ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉ አይደለም፡፡

ሌላዉ የስር ፍርድ ቤት ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 216(3) ድንጋጌ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ አንድ ክስ ክሱን በሚያቀርብበት ጊዜ ከክሱ ጋር አጠቃሎ ማቅረብ ይችል የነበረ የበሰለ የክስ ምክንያት እያለ ሆን ብሎ ነጣጥሎ ያቀረበ እንደሆነ ነዉ፡፡ ነገር ግን በተያዘዉ ጉዳይ ላይ የቀደመዉ ክስ በቀረበበት ወቅት ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የኮንዶሚንየም ቤት ዕጣ አልወጣም፤ ዕጣዉ ሳይወጣ እና የኮንዶሚኒየም ቤቱ ዕጣ የደረሳቸዉ መሆኑ ሳይታወቅ አመልካች ይህን እንደ አንድ የክስ ምክንያት አድርገዉ ከክሳቸዉ ጋር አጠቃለዉ ማቅረብ ሲችሉ ሆን ብለዉ የተዉት ነዉ ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ በመሆኑም ይህም ድንጋጌ የአመልካችን ክስ ዉድቅ ለማድረግ ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም፡፤

በአጠቃላይ አመልካች ለዚህ ክርክር መነሻ ያደረጉት ጉዳይ በቀደመዉ ክስ መሠረት ክርክር ተደርጎበት ዉሳኔ የተሰጠበት አይደለም፤ የክርክሩ ጭብጥ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታም አልነበረም፡፡ ለክሱ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ የተፈጠረዉ የቀደመዉ ክስ በዉሳኔ ከተቋጨ በኋላ በመሆኑም ከቀደመዉ ክስ ጋር ተጠቃሎ መቅረብ ነበረበት ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የአመልካችን ክስ ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናዉ ብይን የፍ/ብ/ሥነ ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 5 እና 216(3) ትክክለኛ አተረጓጎም ያልተከተለ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 164637 ላይ ጥር 09 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 282610 ላይ መጋቢት 12 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 337 መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገባ በማንቀሳቀስ በዋናዉ ጉዳይ አከራክሮ ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

*ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*